# የአፍሪካ ቀንድ፦ በዝግ ስብሰባ የሚካሄዱ ምስክሮች

የታተመበት፦ ሰኞ፣ ጥቅምት 12 ቀን 2026 (በፈረንጆች አቆጣጠር)

ምንጭ፦ Security Council Report

አክሎግ ቢራራ (ዶር)

ጥቅምት 13 የተባበሩት መንግስታት የፀጥታ ምክር ቤት አባላት በአፍሪካ ቀንድ ስላለው ሁኔታ በዝግ ምክክር አካሂደዋል። በሰሜን ኢትዮጵያ የተባባሰውን ሁኔታ ተከትሎ ስብሰባው እንዲጠራ የጠየቀችው አሜሪካ ናት። በተመድ የፖለቲካና የሰላም ግንባታ ጉዳዮች እንዲሁም የሰላም ኦፕሬሽኖች መምሪያዎች (DPPA-DPO) ውስጥ ለአፍሪካ ጉዳዮች የሚመለከቱት ረዳት ዋና ጸሐፊ ማርቲን ኪማኒ ማብራሪያ አቅርበዋል።

ይህ በሁለት ሳምንታት ውስጥ የምክር ቤቱ አባላት በሰሜን ኢትዮጵያ ስለተከሰቱ የቅርብ ጊዜ ክስተቶች የሚወያዩበት ሁለተኛው ጊዜ ይሆናል። በፈረንሳይ ጥያቄ መሠረት አባላቱ መስከረም 30 ላይ ስለ አፍሪካ ቀንድ በዝግ ምክክር ያካሄዱ ሲሆን፣ በዚያም ኪማኒ ማብራሪያ ሰጥተዋል።

ለዚህ ዝግ ስብሰባ አስቸኳይነት ምክንያት የሆነው ምንድን ነው? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ መድፈር ያለብን እኛው ትውልደ ኢትዮጵያን ነን።

የዛሬ ሁለት ሳምንት በኢትዮጵያ ሁከት መጨነቁ ጨናማ ሆኖ ስላላገኘነው እኔና ባለቤቴ ኩራሳው ወደምትባል ሆላንድ የምትቆጣጠራት ደሴት ሂደን ነበር። በጉብኝታችን የታዘብነው አንድ መሰረታዊ ጉዳይ፤ እኛ ለጊዜውም ቢሆን እንርሳት ያልናትን፤ ጠባብ ብሄርተኞችና ተገንጣይ ኃይሎች ሰላም፤ እርጋታ፤ እኩልነት፤ ፍትህና ዲሞክራሳዊ የመንግሥት ስርዓት የነሷትን ኢትዮጵያንና እሴቶቿን  የማይረሱ የኩራሳው ዜጎችና ተቋማት መኖራቸው ነው። ጃማይካዊያን "ራስታ" ነን ሲሉ የሚያንጸባርቁት መንፈስ ኢትዮጵያዊነትን አይደለም?

ለኢትዮጵያ ዘላቂ ብሄራዊ ጥቅም፤ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ክብር፤ ሰብእነት፤ ሰላም፤ እኩልነት፤ ፍትህ፤ ብልጽግና የሚያዋጣን በዘውግ መከፋፈል አይደለም። በጎሳና በቋንቋ የተዋቀረው የፌደራል ስርዓት ብሄረሰቦች ከመቸውም በባሰ ደረጃ እርስ በርሳቸው እንዳይተማመኑ፤ እንዲጋጩ፤ ካለፉት ጥፋቶቻቸው እንዳይማሩ፤ "እኛና እነሱ" ወደሚል ዝንባሌ ገብተው እንዳይታረቁ አድርጓቸዋል። ይህንን የከፋፍለህ ግዛው፤ በለውና ብላው ሁኔታ ካልቀየርነው ኢትዮጵያ የምትባል አገር ልትቀጥል የምትችልበት ሁኔታ እየጠበበ ይሄዳል። ሁኔታውን የሚያባብሱት ደግሞ የኢትዮጵያ የውጭ ጠላቶች ናቸው።

ስለሆነም፤ የዜግነት መለያችን፤ ማለትም፤ ፓን ኢትዮጵያኒዝም (ኢትዮጵያዊነት)  የጋራ እንዲሆን ግዴታችንን የምንወጣበት ወቅት ላይ ደርሰናል።

የሰብሳቢ መርህ ጥሪ

መላውን የኢትዮጵያን ሕዝብ ወክለን ኢትዮጵያን ከመፈራረስ አደጋ ለማዳን የምንችለው የአስተሳሰብ ለውጥ ስናደርግ ብቻ ነው። እንደ ተመድና የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ተቋማት ያሉት ጣልቃ ገብተው ያስታርቁን የሚለው አስተሳሰብ ቢሰራና ቢተገበር ኖሮ ሰላምና እርጋታ ይቻል ነበር። ወሳኙ የኢትዮጵያዊያን ከዘውግ፤ ቋንቋና እምነት በላይ ለመላው ሕዝባችንና ለታሪካዊዋ አገራችን አብረን ለመስራት ስንችል ነው። የውጭ ኃይሎች ሚና የኛን አቅም ለማጠናከር እንጅ ለመተካት ሊሆን አይችልም። የችግሩ ባለቤት እኛው ነን፤ የመፍትሄውም ተጠያቂዎች እኛው ነን። ድር ቢያብር የሚለው ብሂል መተግበር አለበት።

ኢትዮጵያ ዘርፈ ብዙ ችግር ያለባት አገር ናት። በእርስ በርስ ጦርነት እና በመንግሥት መር ሁከቶች የተበከለው

የኢትዮጵያ እኮኖሚ ሥራ ፈጣሪነትና ምርታማነት ከሌሎች በማደግ ላይ ካሉ የአፍሪካ አገሮች ጋር ሲነጻጸር ልዩነቱ የኦህዴድ ብልጽግናው መንግሥት ከሚሰብከው የተለየ ሆኖ ይታያል። በዚህ ወር አይኤምኤፍ ባወጣው ዘገባ መሰረት የኬንያ ጠቅላላ የአገር ውስጥ ገቢ $151 ቢሊየን፤ የጋና **$129** ቢሊየን፤ የኢትዮጵያ **$127** ቢሊየን ነው። የኢትዮጵያ ዝቅ ያለበት ዋና ምክንያት የብር ዋጋ በከፍተኛ ደረጃ እንዲወርድ በመደረጉ ነው። ዐብይ አህመድ “እናታችን” ብሎ የሰየመው አይኤምኤፍ በኢትዮጵያ ላይ የጫነው ፖሊሲ አሉታዊ ውጤት መሆኑ ነው። የኢትዮጵያ ተግዳሮቶች መንግሥት መር፤ መዋቅራዊና ተደራራቢ ናቸው። ከእትዮጵያ ተቋማዊ፤ መዋቅራዊና መንግሥታዊ ተግዳሮቶች መካከል ድህነት አንዱ ነው። ድህነትን በሚመለከት ምክንያቶቹን ባጭሩ ላቅርብ። ኢትዮጵያ ለምን አሁንም በድህነትና በምግብ እጥረት ውስጥ ትገኛለች?

ስድስት ዋና ዋና መንስኤዎች — ጥቅምት 2026

1. የፖለቲካ አለመረጋጋትና ተደጋጋሚ ጦርነቶች፦ ግጭቶች የሰው ሕይወትን ከማጥፋት ባሻገር እርሻን፣ ንግድን፣ መሠረተ ልማትንና ኢንቨስትመንትን ያዳክማሉ።

   የእትዮጵያ ሕዝብ በአገር ውስጥ ተደጋጋሚ ጦርነት ምክንያት ከፍተኛ የማህበረሰባዊ ኢኮኖሚ ቀውስ ተሸካሚ ሆኗል። ድህነትን ለመቅረፍ የሚረዳው ግዙፍ ባጀት ለጦር መሳሪያ ሲውል የሚጎዳው ሕዝቡ ነው። በልማት ላይ ሊውል የሚችል ሀብት ለግጭትና ለዳግም ግንባታ ይውላል። እየሰሩ ማፍረስ ለምን የተለመደ ሆነ?

2. ደካማ አስተዳደር፣ ሙስናና የተቋማት ችግሮች፦ የተጠያቂነት እጥረትና የፖሊሲ አለመረጋጋት የሕዝብ ሀብት በብቃት እንዳይጠቀም ያደርጋሉ፤ ኢንቨስትመንትንና ዘላቂ ልማትንም ያስተጓጉላሉ።

3. ዝቅተኛ የግብርና ምርታማነትና የድርቅ ተጋላጭነት፦ አብዛኛው የገጠር ኢኮኖሚ በዝናብ ላይ ይመሠረታል። የመስኖ፣ የቴክኖሎጂ፣ የማከማቻና የገበያ መሠረተ ልማት እጥረት የድርቅና የጎርፍ ተጽእኖን ያባብሳል። ተደጋጋሚ የእርስ በእርስ ጦርነት የተፈጥሮ ጉዳቶችን አባብሷል።

4. የኢኮኖሚ መዋቅር፣ የሥራ እጥረትና የዋጋ ግሽበት፦ የኢኮኖሚ እድገት በቂ ምርታማ ሥራ አልፈጠረም።

5 . የውጭ ምንዛሬ ችግር፣ የዕዳ ጫናና የዋጋ ግሽበት የቤተሰቦችን የመግዛት አቅም ያዳክማሉ። ምግብ ቢኖርም ሰዎች መግዛት ሊያቅታቸው ይችላል።

   ብድርን በሌላ ብድር መተካት ህብረረሰቡን ይጎዳል፤ እዳውን የሚከፍለው ተከታታይ ትውልድ ነው።

6. የትምህርት፣ የጤናና የሰው ኃይል ልማት እጥረት፦ ደካማ የትምህርት ጥራት፣ የጤና አገልግሎት እጥረትና የሕፃናት የተመጣጠነ ምግብ እጥረት ምርታማነትን ይቀንሳሉ፤ ድህነት ከአንድ ትውልድ ወደ ሌላ እንዲተላለፍም ያደርጋሉ። ብዙ ሚሊየን ወጣት

ትውልድ ከትምህርት ገበታ ውጭ ነው። ለዚህ ተጠያቂ የፌደራሉ መንግሥት ባለሥልጣናትና የክልል አለቃዎች ናቸው።

ማጠቃለያ፦ የኢትዮጵያ ድህነትና ረሃብ የአንድ ምክንያት ውጤት አይደሉም። ዘላቂ መፍትሔ ሰላምን፣ ተጠያቂ አስተዳደርን፣ ዘመናዊ ግብርናን፣ ሥራ ፈጠራንና በሰው ሀብት ላይ ኢንቨስትመንትን ይጠይቃል።

ሰላምና እርጋታ ካለ፤ ሰብአዊ መብት ከተከበረ፤ ሌብነትና ሙስና ህገ ወጥ ከሆነ፤ ለገጠሩ ሕዝብ አቅም ግንባታ ከፍተኛ ትኩረት ከተሰጠ፤ የግሉ ክፍል እንዲስፋፋ አመቻች ሁኔታ ከተፈጠረ፤ ተፎካካሪነት ያለው በሕግ የሚመራ፤ ሕዝብን ያማከለ የእድገት እና የልማት መርህ ከተገበረ ኢትዮጵያ ድህነትን ለመቅረፍ ትችላለች።

ድህነት ባንድ በኩል፤ በሌላ በኩል ሰላም አልባነት ተደራራቢ ተግዳሮቶች ናቸው። ድህነትና ስራ አልባነት ግጭት እና ስደተኛነት ፈጣሪ ናቸው። የኦህዴድ ብልጽግና መንግሥት ይህንን እንደ ተለመደና ቀላል ክሳተት ያየዋል። ሁሉን ነገር በመሳሪያ ኃይል ለማስተካከል ይቻላል የሚል አመለካከት አለ።

ለተጨማሪ መረጃ፦ የዓለም ባንክ (World Bank) እና የዓለም የምግብ ፕሮግራም (WFP) የኢትዮጵያ ሪፖርቶች።

**ወቅታዊ ጥሪ---ኢትዮጵያዊነትን እናስተናግድ (A call for Pan-Ethiopianism)**

ከአሁን በኋላ የምንደራጀውና የምንታገለው የሰው ፍጥረት መሆናችን ተቀብለን፤ እንደ ኢትዮጵያዊ እንጅ እንደ የአንድ ብሄር ወይንም ዘውግ ተወካይ ሆነን አይደለም ወደሚል ምእራፍ መሸጋገር አለብን (It is imperative that we move from the disastrous political framework of tribalism to that of Pan-Ethiopianism)…በዘውግና በቋንቋ ላይ የተመሰረተው የፌደራል ስርዓት በተከታታይ መቅስፍትና ውድመት አከትሏል።

ልንከደው የማንችለው ሃቅ እኛ ኢትዮጵያዊያን ተዋልደናል፤ ተጋብተናል፤ ተዛምደናል፤ አንለያይም፤ ፍትሃዊና ዲሞክራሳዊ መንግሥት የመመስረት ግዴታ አለብን ብለን እንነሳ። ልንለያይ አንችልም ካልን ከብሄራችን በላይ ማሰብና እንደ አንድ አገር ዜጋ፤ ማለትም፤ እንደ ኢትዮጵያዊ ማሰብ አለብን፤ መስራት አለብን።

አንድ መሰረታዊ ጥያቄ ላቅርብ። እያንዳንዳችን አላፊ መሆናችን ከተቀበልን፤ ለተከታታይ ትውልድ ትተነው የምናልፈው እሴት ምን ይሆናል?

ፈረንጆች ሊመልሱልን አይችሉም፤ አይፈቅዱም።

ብዙዎቻችን ኢትዮጵያ የሥልጣኔ መድረክ፤ የጥቁር ሕዝቦች ነጻነት ተምሳሌት፤ የአፍሪካ አንድነት መዲና፤ በተፈጥሮ ኃብቷ፤ በአቀማመጧና በህዝብ ስርጭቷ የምታስቀና ጀግኖች ደማቸውን አፍሠውና አጥንታቸውን ከስክሰው ያስረከቡንን ታላቅ አገር ናት እንላለን። የብሄር ልሂቃን በተከታታይ እያደሚት ነው ግን አንልም፤ አንደፍርም። ሻቢያ፤ ህወሓት እና ኦነግ በጋራ በዘውግ የከፋፈሏትን አገር እኛም መንደርተኛ፤ ቂመኛ፤ ጎጠኛ መሆናችን ሁኔታውን አባብሶታል።

የተባበሩት መንግሥታትን የመሰረተችው ኢትዮጵያ እንቆቅልሽ

የተመድ ትኩረት ለምን ተከሰተ?

የተመድ ተደጋጋሚ አስቸኳይ ስብሰባዎች የሚያሳየው ሃቅ የኢትዮጵያ ሁኔታ ቀጠናዊና ዓለም አቀፋዊ መሆኑን ነው። ብዙ እጆች ገብተውበታል።' የአፍርካ ቀንድ የቀይ ባህር አካል ነው። ኢትዮጵያ የባህር በሯን የተነጠቀችው በህወሓት አመቻችነት እና በኦግ ድጋፍ ነው። ሻቢያ፤ ህየሓትና ኦነግ አማራ ጠል ብቻ አይደሉም። ኢትዮጵያ ጠልም ናቸው። ተገንጣዮች ናቸው። የኦህዴድ ብልጽግናም እኮ አማራ ጠልና ኢትዮጵያ ጠል ነው።

ተመድ ጣልቃ የገባበት ዋና ምክንያት የኢትዮጵያ ተቀናቃይ ኃይሎች የአገራቸውን ችግር ራሳቸው ለመፍታት ስላልቻሉ ነው።

ሆኖም፤ ኃያላን መንግሥታት ሁኔታውን የሚገመግሙት ከራሳቸው ብሄራዊ ጥቅም አንጻር ብቻ ነው። ለዚህ ዋናው ተጠያቂ የኦሮሙማን አጀንዳ የሚያስተጋባው የኦህዴድ ብልጽግና መንግሥት እንጅ የኢትዮጵያ ህዝብ ወይንም የአማራ ፋኖ አይደለም። ትብብር ለህልውና የሚለው እንቅስቃሴ በመሰረታዊ የኢትዮጵጵያ ዘላቂነንትና ኢትዮጵያዊነት ላይ የሚከተለው መርህ ምን እንደሆነ ለኔ ግልጽ አይደለም። ይህን ትብብር በበላይነት የሚመራው ማን እንደሆነም አላውቅም።

ትብብሩ የህወሓትን አጀንዳ የሚያስተናግድ አካል ነው የሚሉ ተመልካቾች አሉ። እነዚህ አካላትና ግለሰቦች ትክክል አይደላችሁም ብሎ ለመከራከር አይቻልም። ምክንያቱም፤ የህወሓት ጸረ ኢትዮጵያዊነት፤ ጸረ አማራነት፤ ሴረኛነት፤ ተንኮለኛነት፤ ተገንጣይነት፤ ተስፋፊነት አሁንም እንዳለ ነው። ህወሓት ማኒፌስቶውን አልቀየረም፤ የቀየረው ዘዴውን ነው።

ጥምረት ወይንስ ጮሌነት?

እርግጥ፤ በሶሻል ሜድያ የሚለፈፈውን ስንገመግም፥ ይህ እንቅስቃሴ ሕዝብ አድን፤ አገር አድን የሚል ህብረብሄራዊ ጉዞ ነው ይሉናል። የመጨረሻ ግቡ ፍትሃዊና ዲሞክራሲያዊ ሃገረ መንግሥት ለመገንባት ከሆነ ኢትዮጵያን ያድሳታል። የመሬት ነጣቂነትና የሥልጣን ሺሚያ ከሆነ የሚደረገው ጉዞ ለኢትዮጵያ ዘላቂነት አደጋ ይሆናል፤ የውጭ አገሮች ጣልቃገብነት ይባባሳል እንጅ አይቀንስም።

የአሁኑን ሁኔታ ያባባሰው የብልጽግናው ከፋፍለህ ግዛው አመራር የአማራው ሕዝብ በኢትዮጵያ ምንን አይነት ፋይዳ ያለው ሚና እንዳይጫዎት መወሰኑ ጭምር ነው። የአማራውን ሕዝብ የኮነነ ወይንም ያገለለ መንግሥት ኢትዮጵያን ሊታደጋት አይችልም።

ይህ አግላይነት በራሱ አገር አፍራሽ ነው። ለዚህ ነው፤ ኢትዮጵያ በዜግነት መብት ላይ የተመሰረተ ሕገ መንግሥት የሚያስፈልጋት። አማራ፤ ትግራይ፤ አፋር፤ ጉራጌ፤ አኗክ፤ ኦሮሞ ወዘተ በየትኛውም ኢትዮጵያ ተከብሮ የሚኖርባት አገር መሆን አለባት ኢትዮጵያ።

የፓን ኢትዮጵያ መንፈስ ይኼው ነው። ለማ መገርሳ የተናገሩት ትክክል ነው። "ኢትዮጵያዊነት ሱስ ነው።" ከደማችን ጋር የተያያዘ መንፈስ ነው። ያዋጣል፤ በመላው ዓከም መድረክ ያስከብራል። በየትኛውም ዓለም ብንሰደድ ኢትዮጵያን ለመርሳት አንችልም። አለመርሳት ብቻውን አገር አያድንም። እንደ ኢትዮጵያዊ ማሰብን ይጠይቃል። ኢትዮጵያን የሚወክል ህብረ ብሄራዊ ተቋም ያስፈልጋል፤ ድርጅት ያስፈልጋል፤ ብቃት ያለው አመራር ያስፈልጋል። ስትራተጅ ያስፈልጋል።

አንድ ምሳሌ ላቅርብ። አማራው ወይንም ትግራዩ ወይንም ኦሮሞው በተናጠል አቤቱታ ሲያቀርብ የማይሰማው ለምን ይመስለናል? በጋራ ብንሰራ ድምጻችን እንደሚሰማ አልጠራጠርም። አንድነት ኃይል ነው።

የህልውና ትግል የሚለው መርህ አግባብ አለው። ምክንያቱም፤ እየለዩ አንድን ብሄር ወይንም እምነት መጨፍጨፍ፤ ማሳደድና ማምከን ጀኖሳይድ ነው። ጀኖሳይድ ሁሉንም ይመለከታል።

የኦህዴድ ብልጽግና መንግሥት ጀኖሳይደር መሆኑ አያከራክርም። ግን የዓለም መንግሥታት ይህንን ሃቅ አያስተናግዱትም። የኛ መበታተን ሁኔታውን አባብሶታል።

የትግራይ ሕዝብ ነፃነት ግንባር (ህወሓት) ከሌሎች ስድስት የታጠቁ ቡድኖች ጋር «የህልውና ጥምረት» የተባለ ጥምረት ከመሠረተ በኋላ፣ በሰሜን ኢትዮጵያ ያለው ውጊያ በመስከረም መጨረሻ ተባብሷል። ጥምረቱ የኢትዮጵያን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድን ከሥልጣን ለማስወገድ እንደሚፈልግ ተገልጿል። መስከረም 23 ደግሞ «የመከላከያ ጦርነት» ውስጥ መሆኑን አስታውቋል። ተቃውሞው መሰረታዊ ለውጥ ለማምጣት ነው ከተባለ ቻርተሩ ምንድን ነው?

**የመጨረሻ ግቡ ግን አሁንም (The end game) ግልጽ አይደለም።**

የሰሜኑን ጦርነት፤ እልቂትና ውድመት እንገምግመው። ይህ ውጊያ በ2020–2022 በትግራይ ክልል በህወሓትና በኢትዮጵያ መንግስት መካከል ከተካሄደው፣ ኤርትራም ከኢትዮጵያ መንግስት ኃይሎች ጎን ተሰልፋ ከተዋጋችበት ጦርነት ወዲህ በአካባቢው ከታየው ሁሉ የከፋ የግጭት መባባስ ነው። ኦፊሴላዊ ቁጥር ባይወጣም፣ በዚያ ግጭት የሞቱት ሰዎች ብዛት ወደ **600,000** እንደሚጠጋ ይገመታል። ለሁለት ዓመታት የቆየው ጦርነት የሰብዓዊ ቀውስም አስከትሏል። በአማራው ሕዝብ ላይ የተካሄደው እልቅት ግን ሲጠቀስ አይታይም። ለዚህ እልቂት ተጠያቂው ማነው? የዓለም መንግሥታት ለምን ቸል አሉት?

በግጭቱ የተሳተፉ ሁሉም ወገኖች ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ሕግንና ዓለም አቀፍ የሰብዓዊነት ሕግን በስፋት ጥሰዋል የሚሉ ክሶችም ቀርበዋል። በሃላፊነት የተጠየቀና ለፍርድ የቀረበ ግለሰብ ወይንም አካል የለም።

በተመሳሳይ ሁኔታ ብቻ ሳይሆን በተደጋጋሚና በከፍተኛ ደረጃ መንግሥት መር የሆነ እልቂትና ውድመት በደረሰበት በአማራው ሕዝብ ላይ ትችት ሲቀርብ አልሰማሁም፤ አላየሁም። ለምን?

ለዚህ የአማራ ምሁራንና ልሂቃን መበታተን ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል።

## የአማራው ሕዝብና የኢትዮጵያ ጠበቃ ማነው?

አንዱ ተግዳሮት በተደጋጋሚ እንዳሳሰብኩት የአማራው ሕዝብ ጠንካራ የሆነ የውጭ ጠበቃ አካል የለውም (A glaring gap in foreign relations and advocacy).

አንዱ የአማራው ችግር ራሱ አማራው ነው። በአማራነቱም ሊሰበሰብ አልቻለም፤ ሊናበብ አልቻለም፤ በኢትዮጵያዊነቱም እንዲሁ። ትችት ያበዛል። መደበቅን ያበዛል።

በቅርቡ የተቀሰቀሰው ግጭት ለወራት እየተከማቸ የመጣ ውጥረትን ተከትሎ ነው። አንዳንድ ተንታኞች የግጭቱን መባባስ በአፍሪካ ኅብረት አሸማጋይነት በኢትዮጵያ መንግስትና በህወሓት መካከል በ2022 የተፈረመው የፕሪቶሪያ ስምምነት ሙሉ በሙሉ አለመተግበሩ ጋር ያያይዙታል። ስምምነቱ የቀጥታ ውጊያውን ያስቆመና ትጥቅ ለማስፈታት ማዕቀፍ የፈጠረ ቢሆንም፣ ለፖለቲካዊ እልባት መንገድ የሚከፍቱ ድንጋጌዎቹ አልተፈጸሙም።

የፕሪቶሪያው ስምምነት የአማራና የኢትዮጵያ አጀንዳ አይደለም።

የፕሪቶሪያው ስምምነት ቢሳካም መሰረታዊ ችግሩን ሊፈታው አይችልም። ወገንተኛነት ያለው ስምምነት ስለሆነ። የአማራውን፤ የአፋሩን ሕዝብ ያገለለ ስምምነት እንዴት ሊሰራ ይችላል?

ጥናቶችና ምርምሮች የሚያሳዩት የትግራይ ልሂቃን፤ ምሁራንና ስብስቦች "በምእራብ ትግራይ" ላይ ያላቸው አቋም ተመሳሳይ ነው፤ ማጠቃለል። ይህ ጉዞ አያዋጣም። የአማራውን አንጡራ መሬት ማጠቃለል ፍትሃዊ አይደለም። ጡብ ይጭራል። አማራውና ትግራዩ በአገር ምስረታ ላይ ከፍተኛ ሚና የተጫዎቱ ህዝቦች ናቸው። ችግራቸውን ተወያይተው እንደሚፈቱት አልጠራጠርም። የብልጽግና መንግሥት የሚፈልገው የአንድ ዘውግ የበላይነት አካልና ተባባሪ መሆን የለባቸውም።

ባጭሩ ይህ ስምምነት ሌሎች ባለድርሻዎችን አላሳተፈም፤ በተለይ አማራውን፤ አፋሩን። በተናጥል የሚደረግ ድርድር ለኢትዮጵያ አያዋጣም። የውጭ መንግሥታትና ተቋማት ኢትዮጵያ ከመፈራረስ ሊታደጓት የሚችሉት ሁሉንም ኢትዮጵያዊያን በማሳተፍና በማስተናገድ ነው።

ኢትዮጵያ ተከባለች

በነሐሴ መጀመሪያ ላይ በሱዳን ድንበር አቅራቢያ በሸረሪና የኢትዮጵያ ብሔራዊ መከላከያ ኃይል (ENDF) እና ህወሓት መካከል ከባድ ግጭት መካሄዱ ተዘግቧል። ሁለቱም ወገኖች ግጭቱን አስጀምሯል በማለት እርስ በርሳቸው ተወነጃጅለዋል። በዚያው ወር በኋላ በትግራይ ዋና ከተማ መቀሌ ላይ በበርካታ ድሮኖች ጥቃቶች ተፈጽመዋል፤ የአካባቢው ባለሥልጣናት ጥቃቶቹን በመከላከያ ኃይሉ ላይ አሳበዋል።

የድሮን ጥቃት በተደጋጋሚ በአማራው ክልል ሲካሄድ ቆይቷል፤ ከትግራይ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ነው ቢባልም፤ ሊካድ የማይቻለው ሃቅ፤ በአማራው ክልል ተደጋጋሚ ጥቃት፤ ውድመት፤ እልቂት ተካሂዷል። አማራውም፤ ትግራዩም የዐብይ ሰራዊት ኢላማ መሆኑ

ሊሰመርበት ይገባል። ህልውናውን የጋራ ትግል የሚያደርገውም ይኼው ብቻ ነው። ሆኖም፤ ከህልውናው ባሻገር ምን ማድረግ አለብን? የሚለውን ጥያቄ ትብብሩ አልመለሰውም። ለምን? በተለይ መመለስ ያለበት የአማራ ፋኖ ብሄራዊ እንቅስቃሴ የበላይ አመራር ነው።

መስከረም 22 የኢትዮጵያ መከላከያ ኃይል በትግራይ ውስጥ አምስት ትምህርት ቤቶችን የመቱ የአየር ጥቃቶችን፣ የድሮን ጥቃቶችንም ጨምሮ፣ እንዳካሄደ ተዘግቧል። በማግስቱ (መስከረም 23) ህወሓት በመቀሌ፣ በአክሱምና በሽሬ ከተሞች የሚገኙ ሦስት አየር ማረፊያዎችን ተቆጣጠረ።

የተመድ የሰብዓዊ መብቶች ከፍተኛ ኮሚሽነር ቮልከር ቱርክ መስከረም 25 በሰጡት መግለጫ፣ የተባባሰው ውጊያ በሲቪሎች ላይ እያስከተለ ባለው ተጽዕኖ እጅግ መጨነቃቸውን ገልጸዋል። በተለይም ህወሓት «ሕፃናትን ጨምሮ ሲቪሎችን በግዳጅ በብዛት የመመልመል ዘመቻውን» መቀጠሉን፣ እንዲሁም «ምልመላውን በሚቃወሙ ሰዎች ላይ ያነጣጠሩ የግድያ፣ የማሰቃየት፣ የዘፈቀደ እስር፣ የግዳጅ መፈናቀልና ሌሎች የበቀል እርምጃዎችን» አውግዘዋል።

ይህ አቀራረብ አድሏዊ ሆኖ አየዋለሁ። የዐብይ መንግሥት የሚፈጽመውን ተደጋጋሚ ወንጀል፤ እልቂት፤ ውድመት ለምን ዝም አሉት? ዐብይ አህመድ በሚያስማራው እየሞተ፤ እየቆሰለና እጁን እየሰጠ ያለው ወጣት ትውልድስ ሰብአዊ ፍጥረት አይደለም? ለዚህ ተጠያቂው ራሱ ዐብይ አህመድና ግብረ አበሮቹ አይደሉም? ወንድም ወንድሙን እንዲገድል የሚያመቻቸው የብልጽግና አገዛዝ አይደለም? ኢትዮጵያን ለውጭ ጠላቶች ጥቃት ያመቻቸው ይኼው አገዛዝ አይደለም? ዐብይ አህመድን የሚጋልበው የኤምሬትስ መንግሥት አይደለም?

“መከላከያ ኃይሉ የመልሶ ማጥቃት ዘመቻ ከጀመረ በኋላ፣ የህልውና ጥምረት ጥቅምት 3 ከመቀሌ መውጣቱን አስታወቀ፤ ከመንግስት ጋር የተሰለፉ ኃይሎችም ወደ ከተማዋ ገቡ። ከዚያ በኋላ ለመንግስት ደጋፊ የሆኑ ኃይሎች እዳጋ ሐሙስ፣ ዓቢይ ዓዲና ዓዲግራትን ጨምሮ በትግራይ ከተሞች ተጨማሪ ግስጋሴ ማድረጋቸውን ዘግበዋል።

መስከረም 23 የአፍሪካ ኅብረት ኮሚሽን ሊቀመንበር ማሕሙድ ዓሊ ዩሱፍ፣ የፕሪቶሪያ ስምምነትን ያስገኘውን የሽምግልና ሂደት የመሩትን የኅብረቱ የአፍሪካ ቀንድ ከፍተኛ ተወካይ ኦሉሴጉን ኦባሳንጆን፣ የታደሱ ዲፕሎማሲያዊ ጥረቶችን እንዲደግፉ ጠየቁ። በመስከረም 26 በተካሄደው የተመድና የአፍሪካ ኅብረት የሰላምና ደኅንነት የጋራ ግብረ ኃይል የምክክር ስብሰባ፣ ሁለቱ ድርጅቶች በሰሜን ኢትዮጵያ በጨመረው ውጥረት «ስጋታቸውን ገልጸዋል»።

በመስከረም 30 በተካሄደው የፀጥታ ምክር ቤት ዝግ ምክክር፣ ኪማኒ ይህ ጉዳይ ጥቅምት 23 በሚካሄደው 20ኛው ዓመታዊ የተመድ ፀጥታ ምክር ቤትና የአፍሪካ ኅብረት የሰላምና ደኅንነት ምክር ቤት የጋራ ምክክር ላይ እንዲነሳ ምክረ ሐሳብ እንዳቀረቡ ይመስላል፤ ሆኖም ጉዳዩ በአጀንዳው ላይ የሚካተት አይመስልም።

የፀጥታ ምክር ቤቱ አባላት የቅርብ ጊዜው መባባስ በሀገራት መካከል ሊፈጥረው በሚችለው ግጭት ላይ የበለጠ እየተጨነቁ ይመስላል። ጭንቀታቸው በኢትዮጵያ ንጹህ ህዝብ ላይ በተካሄደውና በሚካሄደው የሚዘገንን ተደጋጋሚ መንግሥት መር እልቂትና ውድመት አይደለም።

በ2020–2022 ጦርነት ኤርትራ ከኢትዮጵያ መንግስት ኃይሎች ጎን ብትዋጋም፣ ከዚያ ወዲህ የሁለቱ አገራት ግንኙነት ተበላሽቷል። ባለፈው ሳምንት ሁለቱም ወገኖች የየራሳቸውን አቋም የሚገልጹ ደብዳቤዎችን ለምክር ቤቱ ልከዋል። በጥቅምት 9 ደብዳቤ

(S/2026/797) የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ጌዲዮን ጢሞቴዎስ፣ ኤርትራ ሜካናይዝድና እግረኛ ወታደራዊ ክፍሎችን ወደ ኢትዮጵያ ግዛት እንዳስገባች፣ እንዲሁም አማፂ ቡድኖችን እንደምታስታጥቅ፣ ፋይናንስ እንደምታደርግና እንደምትመራ ከሰዋል። በተጨማሪም የተመድ ቻርተር አንቀጽ 51ን በመጥቀስ፣ ኢትዮጵያ በተፈጥሮ ያላትን ራስን የመከላከል መብት ተጠቅማ በኤርትራ ላይ እርምጃዎች እየወሰደች መሆኑን ለምክር ቤቱ አሳውቀዋል።

በጥቅምት 10 የምላሽ ደብዳቤ (S/2026/798) የኤርትራ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዑስማን ሳልሕ፣ የራስን መከላከል ጥያቄ የወረራ ጦርነትን ለማስረዳት የቀረበ ሙከራ ነው በማለት ውድቅ አድርገውታል። ኢትዮጵያ «በባለቤትነት የሚተዳደር የባሕር መዳረሻ» በኃይል ለማግኘት እንደምትፈልግም ከሰዋል። በደብዳቤያቸው የኢትዮጵያ ምክትል ኤታማዦር ሹም ጄኔራል አበባው ታደሰ መስከረም 27 መቀሌ ኤርትራን ለመውረር በሚደረግ ጉዞ ላይ «የመካከለኛ ማረፊያ» ናት ብለው የተናገሩትን ጠቅሰዋል። ሳልሕ ምክር ቤቱ የኢትዮጵያን

«የጦርነት አዋጅ» እንዲያወግዝና በቻርተሩ ምዕራፍ VII መሠረት የመከላከያ እርምጃዎችን እንዲወስድ ጠይቀዋል።

## የባህር በር ማዘናጊያ መሆን የለበትም

ኢትዮጵያ የባህር በር የሚያስፈልጋት መሆኑን እደግፋለሁ፤ ጥያቄው ለምን ሳይሆን እንዴት? የሚለው ነው። በድርድር፤ በዲፕሎማሳውዊ ውይይትና በጋራ ተጥቃሚነት (Mutual benefit) እንዲሆን አሳስባለሁ።

ለኤርትራም ሆነ ለኢትዮጵያ በዘላቂነት የሚያዋጣቸው በፌደሬሽን አንድ አገር መሆን፤ ወይንም የጋራ ገበያ መመስረት ነው። የኢትዮጵያ የባህር በር ለኤርትራም ይጠቅማል እንጅ አይጎዳም። ይህ በስምምነት መደረግ አለበት።

ኢትዮጵያ አሥር ኤርትራዊ ዲፕሎማቶችን ካባረረችና በአሥመራ ያለውን ኤምባሲዋን ከዘጋች በኋላ፣ ኤርትራ ጥቅምት 1 ከኢትዮጵያ ጋር ያላትን ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት አቋረጠች። ዐብይ አህመድ የኖቤል ሽልማቱን ያገኘበትን ምክንያት ወደ ጎን ትቶታል። የሁለቱም አገሮች የበላይ መሪዎች ለሕዝባቸው የሚያስቡ አይመስሉም።

የቀጠናው የኃይል አሰላለፍ ስትራተጅክ ለውጥ

ጥቅምት 4 የግብፅ፣ የኤርትራ፣ የሱዳንና የሶማሊያ መሪዎች ተገናኝተው የኤል አላሜይን የጋራ መግለጫን አጽድቀዋል። በመግለጫው የቀይ ባሕር አስተዳደር የባሕሩ ዳርቻ ያላቸው አገራት ብቻ ኃላፊነት መሆኑን አረጋግጠዋል። ይህንን ውሳኔ በበኩሌ አልቀበለውም፤ ኢትዮጵያን ያገለለ በመሆኑ። በተመሳሳይ ግን የኦህዴድ ብልጽግና መንግሥት መላውን የኢትዮጵያን ህዝብ በሚገዛው የኤምሬትስ ድሮን እየደበደበ ፤ በአዲስ አበባ ለመኖር ፈተና በሆነበት ወቅት “ቀይ ባህር የሚል ማዘናጊያ ሲወረውር ይገርመኛል። ለማን ጥቅም ብሎ ነው? የሚል ጥያቄ አግባብ አለው።

ኢትዮጵያ የባህር በር መብቷ የሚከበርበት ወቅት እንደሚመጣ አልጠራጠርም። መጀመሪያ የአገር ውስጥ ሰላምና እርጋታ ይመስረት፤ የአሁኑ የእርስ በእርስ ጦርነት ግን ይህንን ስኬታማ ለማድረግ የሚያስችልበት መንገድ አይታይም።

ሁኔታውን የቀየረው የአሜሪካ መንግሥት ለኤርትራ መንግሥት የሰጠው እውቅና ነው። የአሜሪካው የውጭ ጉዳይ አለቃ ማርኮ ሩቢዩ መንግሥታቸው በሉዓላዊ አገር “ጣልቃ ገብነትና ሌላ ጦርነት አያስፈልግም” ብለው ሲናገሩ የኢትዮጵያን መንግሥት ማስጠንቀቃቸው መሆኑ ግልጽ ነው። የሚቀጥለው እርምጃ ሁለቱን አገሮች ማስታረቅ ይሆን?

በተጨማሪ፤ ማርኮ ሩቢዮ ህወሓትንና ለሎቹን የጥምረቱ አባላት ከመተቸት አልፈው አጥፊዎች፤ “ተገንጣዮችና ሽብርተኞች” ብለው ኮንነዋቸዋል። የአማራ ፋኖ የጥምረቱ አካል ስለሆነ ይመለከተዋል ማለት ነው። ሩቢዮ የኦህዴድ ብልጽግናውን መንግሥት አልተቹም።

ለምን ይሆን?

የአማራ ፋኖ የበላይ አመራር በፍጥነት የተለዋወጠውን የቀጠናውን የኃይል አሰላለፍ እንደምታ—ጥቅሙን፤ ጉዳቱን፤ እድሉን ወዘተ—መገምገም አለበት። የዳበሳ ጉዞ ለአማራውም ሆነ ለኢትዮጵያ አያዋጣም።

ጥቅምት 5 ለሌላ የአምስት ዓመት የሥልጣን ዘመን ቃለ መሐላ በፈጸሙበት ወቅት ዐቢይ፣ የባሕር ዳርቻ የሌላት ኢትዮጵያ ወደ ቀይ ባሕር መዳረሻ ሊኖራትና ስለ ቀይ ባሕር ደኅንነት በሚካሄዱ ውይይቶች ውስጥ ልትካተት እንደሚገባ በድጋሚ ተናግረዋል። የአፍሪካ ኅብረት ኮሚሽን ኢትዮጵያ፣ ኤርትራና ግብፅ ከፍተኛ ጥንቃቄና ራስን መግታት እንዲያሳዩ ጥሪ አቅርቧል።

በOctober 13 ስብሰባ ኪማኒ፣ የተመድ ዋና ጸሐፊ አንቶኒዮ ጉቴሬዝ ጥቅምት 9 በሰጡት መግለጫ ያነሱትን ነጥቦች አስተጋብተዋል። ጉቴሬዝ በትግራይ፣ በአፋርና በአማራ እንደገና በተቀሰቀሰው ውጊያ እጅግ እንደተጨነቁ ገልጸው፣ ግጭቱ ወዲያውኑ እንዲቆምና በፕሪቶሪያ ስምምነት መሠረት ወደ ውይይት እንዲመለሱ ጠይቀዋል። በኢትዮጵያ ውስጥ የኤርትራ ኃይሎች መኖራቸውን የሚጠቁሙ ሪፖርቶችም አሳስበዋቸዋል።

ሀገራት ኃይል ከመጠቀም ወይም በኃይል ከማስፈራራት እንዲቆጠቡ በተመድ ቻርተር ያለባቸውን ግዴታ አስታውሰው፣ የማሸማገል አገልግሎታቸውን ለማቅረብ ዝግጁ መሆናቸውን ገልጸዋል። ኪማኒ በ2000 በኤርትራና በኢትዮጵያ መካከል የነበረውን ግጭት ያቆመውን የአልጀርስ ስምምነትም ጠቅሰዋል። ጉቴሬዝ በታኅሣሥ 2025 ስምምነቱ 25 ዓመት መሙላቱን በሚያስታውስ መግለጫ፣ ሁለቱ አገራት ለዘላቂ ሰላም ያለውን ራዕይና በስምምነቱ የተንጸባረቀውን «የሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት አክብሮት» እንደገና እንዲያረጋግጡ ጠይቀዋል። ኪማኒ ተመሳሳይ መልዕክቶች አቅርበዋል።

የምክር ቤቱ አባላት በቅርቡ በይፋ የሰጧቸውን መግለጫዎች የሚያንጸባርቁ አቋሞችን አቅርበዋል። ለምሳሌ፣ እንግሊዝ የህልውና ጥምረት «የኢትዮጵያን መንግስት ለመገልበጥ ያለውን የተገለጸ ዓላማ» ውድቅ አድርጋለች። ፈረንሳይና ሌሎች የአውሮፓ አባላት የጥምረቱን ጥቃቶች አውግዘው፣ ውጥረቱን ለማርገብ የሚያስችል ተዓማኒ መንገድ እንዲኖር ድጋፋቸውን ገልጸዋል። ዋናውን የውስጥ መሰናክል መንስኤዎች ግን ወደ ጎን መተዋቸው ያስተቻቸዋል (They left the root (systemic and structural) causes of the Ethiopian crisis alone).

የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መምሪያ ግጭቱ አሜሪካ ከኢትዮጵያና ከኤርትራ ጋር ያላትን ትብብር አደጋ ላይ እንደሚጥል ገልጿል። የአሜሪካ ለአረብና ለአፍሪካ ጉዳዮች ከፍተኛ አማካሪ ማሳድ ቡሎስ፣ ሁለቱ አገራት የእርስ በርስ ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት እንዲያከብሩና ከፍተኛ ራስን መግታት እንዲያሳዩ አሳስበዋል።

ሩሲያ በበኩሏ ተፋላሚ ወገኖች የተኩስ አቁም እንዲያከብሩና ውጫዊ አካላት በኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ከመግባት እንዲቆጠቡ ጠይቃለች።

በአጠቃላይ አባላት ግጭቱ ወደ ክልላዊ ጦርነት ሊስፋፋ በሚችልበት አደጋ ስጋታቸውን እንደሚገልጹ፣ ሁሉም ወገኖች ውጥረቱን እንዲያረግቡ እንደሚጠይቁና ሉዓላዊነትንና የግዛት አንድነትን ማክበር እንዲሁም በውይይት መፍትሔ መፈለግ አስፈላጊ መሆኑን እንደሚያሳስቡ ይጠበቃል። ብዙ አባላት በኢትዮጵያ ውስጥ የኤርትራ ወታደሮች መኖርን በሚመለከቱ ሪፖርቶችና ኢትዮጵያ እየወሰደች ነው ስለምትላቸው የራስን መከላከል እርምጃዎች ባህሪ ተጨማሪ መረጃ ሊጠይቁ ይችላሉ። ስለ ሰብዓዊ ሁኔታውም ጥያቄዎች ሊያነሱ ይችላሉ። የተመድ የሰብዓዊ ጉዳዮች ማስተባበሪያ ጽሕፈት ቤት

(OCHA) በግጭቱ ግንባሮች አካባቢ ያለውን የፀጥታ እጦትና የእርዳታ መዳረሻ ላይ ያለውን ቀጣይ እርግጠኝነት ማጣት አጉልቶ አሳይቷል። መፍትሄውስ?

ቀውሱን ለመፍታት የፀጥታ ምክር ቤቱ ሊኖረው በሚገባው ሚና ላይ አባላቱ ሊለያዩ ይችላሉ። አንዳንዶቹ ጉዳዩ በአፍሪካ ኅብረትና በፕሪቶሪያ ማዕቀፍ በኩል እንዲታይ ሊመርጡ ይችላሉ፤ ሌሎች ደግሞ የምክር ቤቱን የበለጠ ጠንካራ ተሳትፎ ሊደግፉ ይችላሉ። የበለጠ ተሳትፎ የሚፈልጉ አባላት እንደ የፕሬስ መግለጫ ያለ የምክር ቤቱ ውጤት እንዲወጣ ድጋፍ ሊገልጹ ይችላሉ።

በ2020–2022 ጦርነት ወቅት በምክር ቤቱ ውስጥ በነበሩ የተለያዩ አቋሞች ምክንያት አባላቱ በትግራይ ሁኔታ ላይ መደበኛ የምክር ቤት ሰነድ ለማውጣት መስማማት ከባድ ነበር። በሚያዝያና በኅዳር 2021 ሁለት የፕሬስ መግለጫዎችን ብቻ ማውጣት ችለዋል። በመግለጫዎቹ ያለ እንቅፋት የሰብዓዊ ድጋፍ መዳረሻ እንዲኖር ጠይቀው፣ «ለኢትዮጵያ ሉዓላዊነት፣ ለፖለቲካዊ ነፃነት፣ ለግዛት አንድነትና ለአገሪቱ አንድነት ያላቸውን ጽኑ ቁርጠኝነት» በድጋሚ አረጋግጠዋል።

በ October 13, በተካሄደው የተመድ አስሸኳይ ዝግ ስብሰብ ምን ድምዳሜ ላይ ተደረሰ?

የተመድ ጭንቀት ይገባኛል። ቢያንስ ቢያንስ የቀጠናውን አደጋ ዘግቧል። በሚከተሉት ሃሳቦች ላይ ስምምነት ተደርሷል።

"የተባበሩት መንግሥታት የጸጥታ ምክር ቤት — የአፍሪካ ቀንድ ቀውስ

የተመለከተው ቀን፦ ጥቅምት 13፣ 2026 (October 13, 2026)

አስፈላጊ ማብራሪያ፦ ስለ ውይይቱ የተገለጸው መረጃ ውስን ነው። የሚከተሉት በውይይቱ ዙሪያ የተጠቀሱ ጭብጦችና ከዚያ በፊት የተሰጡ የሰላም ጥሪዎች ማጠቃለያ ናቸው፤ በጸጥታ ምክር ቤቱ በይፋ የጸደቁ ውሳኔዎች እንደሆኑ መወሰድ የለባቸውም።

1. ግጭቶችን ማቆም፦ ተፋላሚ ወገኖች ከወታደራዊ እርምጃ እንዲቆጠቡና የንግግር መንገድን እንዲከተሉ።

2. የፕሪቶሪያ ሰላም ስምምነት፦ በ2022 የተፈረመውን ስምምነት በተሟላ መልኩ ማስፈጸም።

3. የኢትዮጵያ–ኤርትራ ውጥረት፦ ውጥረቱ ወደ ሰፊ ክልላዊ ግጭት እንዳይሸጋገር ዲፕሎማሲን ማጠናከር።

4. ሉዓላዊነት፦ የሀገራትን የግዛት አንድነት ማክበርና ጣልቃ ገብነትን ማስወገድ።

5. ሰብዓዊ እርዳታ፦ ሲቪሎችን መጠበቅና ምግብ፣ መድኃኒትና ሌሎች አስፈላጊ ድጋፎች እንዲደርሱ ማድረግ።

6. የአፍሪካ ኅብረት ሚና፦ በሰላም ሂደትና በስምምነት ትግበራ ውስጥ ያለውን ሚና ማጠናከር።

7. የጸጥታ ምክር ቤት ቀጣይ ሚና፦ የተመድ ተሳትፎን ከአፍሪካ ኅብረት ጥረቶች ጋር እንዴት ማስተባበር እንደሚቻል ማጤን።"

ይህ ከዝግ ስብሰባ የተገኘ ኦፊሴላዊ የውሳኔ ዝርዝር አይደለም።

**ለማጠቃለል፤**

1. በኔ ግምገማ የኢትዮጵያ የውስጥ መንግሥት መር እልቂትና ውድመት የሚያስተጋባ የአገዛዝ ሁኔታ ካልተፈታ በስተቀር የአፍሪካ ቀንድ ሁከት የሚስፋፋበትና ቀጠናዊ የሚሆንበት እድል ከፍ ያለ ነው። ብዙ የውጭ እጆች ገብተውበታል።

የብልጽግናው አገዛዝ ከሁሉም የጎረቤት አገሮች ጋር ተናክሷል፤ ተጋጭቷል። አመራሩ ጭፍን ነው። ጦረኛነትን ያነገበ ነው። ጀኖሳይደር ነው።

የምእራብ መንግሥታትና ሚድያዎች ባይዘግቡትም የኦህዴድ ብልጽግና መንግሥት ህጻናትን፤ እርጉዝ ሴቶችን፤ ሽማግሌዎችን፤ ትምህርት ቤትና የጤና ጣቢያዎችን፤ ቤተ ክርስቲያንን፤ ሞስክን ወዘተ ሳይለይ በድሮን ይጨፈጭፋል። ከታች ለናሙና የቀረበውን የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በጎንደር የድሮን ጭፍጨፋ እዩና ፍረዱ።

የአሜሪካ መንግሥት ባለሥልጣናት ራሳቸውን መጠየቅ ያለባቸው ሃቅ ሺብርተኛው ማነው? የሚለውን ነው። ሽብርተኛው የኦህዴድ ብልጽግና መንግሥት ሌላውን ሽብርተኛ ነው ብሎ ይከሳል፤ ኃያልን መንግሥታት እውነቱን ከውሸቱ ሳያጣሩ የችግሩ አካል ሆነዋል።

2. የኢትዮጵያ መከላከያ ኃይል የብልጽግና መንግሥት አገልጋይ እንጂ የኢትዮጵያን ግዛታዊ አንድነትና ሉዓላዊ ጥቅም አስከበረ ሆኖ አላየውም። የማን አገር መከላከያ ነው የራሱን ወገን በከባድ መሳሪያ፤ በድሮን፤ በጀት፤ በታንክና ሌላ መሳሪያ የሚጨፈጭፈው? የዐብይ አህመድ መንግሥት ሁል ጊዜ ማዘናጊያ ይለግሰናል። በአሁኑ ወቅት ዋናው ማዘናጊያ የባህር በር ሆኗል።

የባህር በር አስፈላጊነቱ አያከራክርም። ሆኖም፤ አብዛኛው ህዝብ የጠላውና የናቀው የብልጽግና መንግሥት ሌላው ቀርቶ ሕዝቡ ከአዲስ አበብ ወደ ባህር ዳር ወዘተ በሰላም ለመጓጓዝ የሚችልበትን ሁኔታ ለመፍጠር አልቻለም። የአገር ውስጥ ሰላም ስለሌለ ነው።

3. የምእራብ ኃያላን መንግሥታት በተለይ የአሜሪካ መንግሥትና የአውሮፓ የጋራ ማህበር፤ የሩሲያ መንግሥት የኢትዮጵያንና የኤርትራን መንግሥታት ለማስታረቅ የጀመሩትን ጥረት እደግፋለሁ። ሁለቱም አገሮች የሚያቀጣቸው በመልካም ጉርብትና የተመሰረተ ግንኙነት እንጅ የውክልና ጦርነት ሊሆን አይችልም። የኤርትራ መንግሥት ማመን ያለበት ከግብጽ ይልቅ ኢትዮጵያ እንደምትጠቅመው ነው። በተመሳሳይ፤ የኢትዮጵያ መንግሥት ማመን ያለበት ከኤምርቱስ ወዳጅነት ይልቅ በብዙ መስፈርት የኤርትራ ወዳጅነት ዘላቂ ጥቅም እንዳለው ነው።

4. የአሜሪካ መንግሥትና የአውሮፓ መንግሥታት የፕሪቶሪያን ስምምነት ስኬት አጉልተው ማቅረባቸው አያስገርምም። ስምምነቱ እንዲሳካ የሚሞክሩት የአሜሪካ ባለሥልጣናት ናቸው። እነዚህ ባልሥልጣናት ወዳጅና ታማኝ ነው ብለው የፈረጁት ህወሓትን ነበር፤ አሁንም ነው። ይህ ስምምነት ሁሉንም ባለድርሻዎች አላሳተፈም። ዋናው ግብ የአማራውን መሬት፤ በተለይ ወልቃይትን ለህወሓት እና አጋሮቹ ለማስመለስ ነው። በዚህም ምክንያት፤ የፕሪቶሪያው ስምምነት ቢተገበር ችግሩን አይፈታውም።

5. ኢትዮጵያ የባህር በር ያስፈልጋታል። ሆኖም፤ የብልጽግናው መንግሥት የባህር በርን አግባብነት ከመተረኩ በፊት በአገር ውስጥ ሰላምና እርጋታ ላይ ትኩረት ማድረግ አለበት። ኢትዮጵያዊነትን መቀበል አለበት። ግን አያደርግም፤ ጦርነት የሥልጣን መሳሪያ ሆኗል።

6. የአማራ ፋኖና የበላይ አመራር ከፍተኛና አስቸኳይ ትኩረት ማድረግ ያለበት በውስጥ አንድነቱ ላይ ነው። ከሌሎች አጋሮቹ ጋር በአንድ ድምጽ የውጭ ግንኙነታቸውን ለመተግበር የሚቻለው ራሱ የአፋብን የበላይ አመራር አንድ ሲሆን ብቻ ነው። የትብብሩ አቀንቃይ ወይንም አሸከር ከሆነ ለአማራው ፋይዳ ያለው ስራ ሊሰራ አይችልም።

7. ዝንጀሮ መጀመሪያ መቀመጫየን እንዳለችው፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚመኘው የአገር ውስጥ ሰላምና እርጋታ ነው። የብልጽግና መንግሥት ይህን ምኞት አይተገብረውም። ሥልጣኑን የሚያራዝመው በጦርነት፤ ሕዝብን ከሕዝብ ጋር በማናከስ ስለሆነ። ዋናው ግቡ የኦሮሙማን አጀንዳ ስኬታማ ማድረግ መሆኑን አሰምርበታለሁ።

8. ለዚህ የሚያቀጣው ደግም የተቃዋሚ ኃይሎች የዓላማ ጽናት፤ አንድነት እና ከብልጽግናው አገዛዝ የተሻለ የፖለቲካ ፍኖተ ካርታ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሲያቀርቡ ነው።

9. ኢትዮጵያ ብሄራዊ፤ ሁሉን አሳታፊ የሆነ የሽግግር መንግሥት ያስፈልጋታል።

## የምንጭ መረጃና ማጣቀሻዎች

ይህ ጽሑፍ ለሚዲያ አጠቃቀም ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ የተተረጎመ ነው። በጽሑፉ ውስጥ ያሉ ክሶች፣ ግምቶችና የተነገሩ አቋሞች ምንጮች መግለጫዎች ናቸው፤ የተርጓሚው ገለልተኛ ማረጋገጫ አይደለም።


**1.** ጥምረቱ መመሥረት — https://www.euronews.com/2026/09/28/tigray-rebels-push-into-afar-as-ethiopia-blames-neighbours **2.** የሞት ቁጥር ግምት — https://www.ft.com/content/2f385e95-0899-403a-9e3b-ed8c24adf4e7?syn-25a6b1a6=1

**3.** የመብት ጥሰቶች ሪፖርት — https://reliefweb.int/report/ethiopia/report-international-commission-human-rights-experts-ethiopia-ahrc5146-advance-unedited-version

**4.** የፕሪቶሪያ ስምምነት ትንታኔ — https://theconversation.com/ethiopias-peace-deal-is-unravelling-what-went-wrong-with-the-tigray agreement-293005

**5.** የፕሪቶሪያ ስምምነት — https://peacemaker.un.org/en/node/10038

**6.** ሽረሪና ግጭቶች — https://www.bbc.com/news/articles/cdrv6r3xgyeo

**7.** መቀሌ የድሮን ጥቃቶች — https://addisstandard.com/drone-strikes-in-two-locations-in-mekelle-13-casualties-received-at-ayder-hospital/

**8.** የተመድ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ — https://www.ohchr.org/en/press-releases/2026/09/ethiopia-turk-alarmed-civilian-impact-hostilities urges-de-escalation

**9.** ከመቀሌ መውጣት — https://apnews.com/article/ethiopia-eritrea-tigray-conflict-mekelle-un-abiy-9386a16a06e537a29ffe2de273267c8b

**10.** የጦር ግስጋሴ ሪፖርት — https://www.aljazeera.com/amp/news/2026/10/11/ethiopia-eritrea-ramp-up-rhetoric-are-they-inching-towards war

**11.** የአፍሪካ ኅብረት መግለጫ — https://au.int/sites/default/files/PR-%20AUC%20CHAIRPERSON%20CALLS%20FOR%20UTMOST%20RESTRAINT%20AND%20IMMEDIATE%20DE ESCALATION%20IN%20NORTHERN%20ETHIOPIA-En.pdf

**12.** የተመድ–አኅ የጋራ መግለጫ — https://www.peaceau.org/en/article/joint-communique-of-the-twenty-seventh-consultative-meeting-of-the united-nations-african-union-joint-task-force-on-peace-and-security-held-on-26-september-2026-new-york-usa

**13.** የዲፕሎማሲ ግንኙነት መቋረጥ — https://www.reuters.com/world/africa/eritrea-says-it-is-severing-all-diplomatic-ties-with-ethiopia-2026- 10-01/

**14.** የዲፕሎማቶች ማባረር — https://www.bbc.com/news/articles/crpd0d0jl0y0o

**15.** የኤል አላሜይን መግለጫ — https://www.aljazeera.com/news/2026/10/5/four-african-leaders-issue-joint-declaration-as-ethiopia-war escalates

**16.** የቀይ ባሕር መዳረሻ አቋም — https://www.arabnews.com/world/ethiopia-again-demands-access-to-the-red-sea-as-tensions-with neighbors-escalate-3004761

**17.** የአፍሪካ ኅብረት ጥሪ — https://au.int/sites/default/files/PR-%20STATEMENT%20OF%20THE%20AU%20COMMISSION%20ON%20THE%20ESCALATING%20TENSIONS%20BETWEEN%20ETHIOPIA%2C%2 0ERITREA%20AND%20EGYPT.pdf

**18.** የአልጀርስ ስምምነት ዓመታዊ መግለጫ — https://www.aa.com.tr/en/africa/un-chief-calls-on-eritrea-ethiopia-to-respect-border-pact-on-its 25th-anniversary/3769055

**19.** የእንግሊዝ መግለጫ — https://www.gov.uk/government/news/uk-statement-on-escalation-in-northern-ethiopia-24-september

**20.** የፈረንሳይ መግለጫ — https://www.diplomatie.gouv.fr/en/presse-et-ressources/decouvrir-et-informer/actualites/ethiopie-degradation de-la-situation-dans-la-region-du-tigre

**21.** የአሜሪካ መግለጫ **—** https://www.state.gov/releases/office-of-the-spokesman/2026/10/u-s-statement-on-increased-tensions-between ethiopia-and-eritrea

**22.** የማሳድ ቡሎስ መልዕክት **—** https://x.com/US_SrAdvisorAF/status/2107091419290911200

**23.** የሩሲያ መግለጫ **—** https://afrinz.ru/en/2026/09/russia-monitoring-situation-in-ethiopia-with-concern-zakharova/ **24.** የ**OCHA** የሰብዓዊ እርዳታ መረጃ **—** https://www.unocha.org/news/todays-top-news-ukraine-sudan-ethiopia-occupied-palestinian-territory **25.** የ**2021** ሚያዝያ የፕሬስ መግለጫ **—** https://press.un.org/en/2021/sc14501.doc.htm

**26.** የ**2021** ኅዳር የፕሬስ መግለጫ **—** https://press.un.org/en/2021/sc14691.doc.htm

October 21, 2026